# አዲሲቱን ኢትዮጵያዊነት እንፍጠር ስንል...

በእውቀቱ ሲንጅ 04-11-17

ማንም ቢሆን በተናጠል ብቻውን ሆኖ ስለ አንድ ጥያቄ ሲያስብ ከሃሳቡ ጋር ሙሉ በሙሉ የተዋሃደውን እና ከዚሁ አመለካከት ውጭ ማሰብ  የማይቻለውን የሚመርጥበት ዋናው ምክንያት በውስጣችን ባለው መሰረታዊ እምነት የተነሳ ነው፡፡ማናችንም ቢሆን አዳዲስ ሃሳቦችን ለማመንጨት ከሌላው ለመቀበል የራስ እምነት ለማድረግ ከሌላውም ጋር ለመከራከር የነበሩትን ለማዳበር ወይም የቆዩትንም ሃሳቦች ቢሆን ፉርሽ ለማድረግ በተጨባጭ መረጃ በመነሳት ሲሆን ወደዚህ  የሃሳብ  ልእልና ደረጃ ለመድረስና በውስጣችን እንዲሰርጽ የመጣንበት መንገድና ያለው ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ሊገባ የሚችል ነገር ነው፡፡በቅድሚያ የአስተሳሰብ ልእልና ስንል በእይታችን ዙሪያ ሁላችንም አንድ ዓይነት መዝሙሮችን እንድንዘምር፣ስለአንደ ነገር ብቻ መፈክር እንድናሰማ ነገር ግን ከዚህ ውጭ ሊያስብ፣ ሊጽፍ፣ ሊተነትን ለሚፈልግ ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲታፈን ማድረግ ማለት አይደለም፡፡እንዲያውም በቂ ምክንያት ከሌለ በቀር ይህ የአስተሳሰብ ልእልና እንዳይረጋገጥና እንዳይመጣ የለየለት የጥፋት መንገድ መሆን አለበት፡፡

አንድ የተሳሳተና ኋላቀር አስተሳሰብ የሚሸነፈው ስለተሸፈነ ወይም ስለተደበቀ ሳይሆን በይፋ ተገልጾ፣ተጋልጦና ተንገዋሎ ከሰው አእምሮ ሲወገድ ብቻ ነው፡፡ይልቁንም ሃሳቡ የተደበቀ ወይም የተሸፈነ እንደሆነ ኋላቀርነቱን፣ጎጂነቱን በይፋ አውጥቶ ለማጋለጥና ከሰው አእምሮ ለመሰረዝ እጅግ አስቸጋሪ መሆኑ አይቀርም፡፡ለአንድ ትልቅ ሃሳብና ፈጠራ የመጀመሪያ ምንጩ ሊሆን የሚችለው አንድ ግለሰብ ነው፡፡የተገኘው ሃሳብ ወይም ፈጠራ ደግሞ ተግባር ላይ መዋል የሚችለው በህብረተሰቡ ወይም በሚመለከታቸው ሲደገፍ ወይም ሃሳቡ ጠቃሚ፣ አማራጭና ተቀባይነት ሲኖረው ነው፡፡

ስለዚህ ሃሳቦች በነጻ መቅረባቸውና መንሸራሸራቸው ሁሉም ሰው በውስጡ ያሉትን ሃሳቦች ወደ መድረክ አውጥቶ አንዱ ከሌላው በተሻለው ሃሳብ እየተተካ ሲሄድ ነው የአስተሳሰብ ልእልና ሊፈጠር የሚችለው፡፡ይህ የሃሳብ ልእልና በተራዘመ፣የዳበረና የተወሳሰበ ትግል እስኪረጋገጥ መልክ ቅርጽና ይዘታቸው የተለያዩ ችግሮችና እንቅፋቶች እንደሚያጋጥሙት የተረጋገጠ ነው፡፡

በአፈ-ታሪክና ህዝብን በማጭበርበር ሳይሆን ይምረርም ይጣፍጥ በጥሬ ሃቅና ከዚህ በሚመነጭ ትንተና መመስረቱ ተገቢ ነው፡፡እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ህዝቦች ባንድ ወቅት በዓለም የሰለጠኑ ከሚባሉት ህዝቦች ጋር የሚመጣጠን ስልጣኔ ገንብተው እንደነበር እስካሁንም ያልጠፉ የታሪክ አሻራዎች የሚመሰክሩትና የሚያረጋግጡት ሃቅ ነው፡፡አኩሪ ስልጣኔያችን ከስሞ ኢትዮጵያ የድህነት፣የረሃብ፣የጦርነትናብጥብጥ ተምሳሌት ሆና የምትወሰድበትና በስልጣኔ እጅግ ወደኋላ ከቀሩት አሮች ጋር የምትመደብበት ሁኔታ መፈጠሩም ያለንበት ሁኔታ የሚመሰክረው ጉዳይ ነው፡፡ኢትዮጵያ ከዚህ አስከፊ ሁኔታ ተላቃ ማየት የማይፈልግ ኢትዮጵያዊ አለ ማለት አይቻልም፡፡ጤነኛ ካልሆነ ሰው በቀር ማናችንም እንደጥንቱ ከሰለጠኑ አገሮች ተርታ ተሰልፈን ማየትን የማይጓጓ የለም፡፡

አገራችን በስልጣኔ ወደ ኋላ የቀረችው በውስጧ ያቀፈችውን ብዝሃነት በብቃት ማስተናገድ ተስኗት በማያባራ ቀውስና ግጭት ስትናጥ ስለነበረ ነው፡፡በተጨማሪም በድህነት አዙሪት እንድትዳከር ያደረጉ መሰረታዊ ምክንያቶች ተለይተው እነዚህን ለማስወገድ በተመረጠና ውጤታማ አኳኋን የሚንቀሳቀስ መንግስት መመስረትና ማስቀጠል ስላልቻለች ነበር፡፡ድህነት ህዝቡን

በምሬት ወደ ጥፋት መንገድ ሊያመራው ስለሚችል፣ለኋላቀርነት ተጋልጦ የማንኛውም ጸረ-ሰላም ኃይል መጠቀሚያ እንዲሆን ሊያደርገው ስለቻለ የጦርነትና ብጥበጥ ምንጭ በመሆኑ ነው፡፡በመሰረቱ ልማት የህልውና ጥያቄ እንደሆነ የሚታመነው ህዝብን ወይም ማንኛውንም የውጪ ኃይል ስለተፈራ ወይም ስለተጠረጠረ አይመስለኝም፡፡ድህነታችን የመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ እጦት ሊበትነንና እርስ በእርስ ሊያናቁረን ይችላል በሚል ግንዛቤ ከጎረቤት አገሮችና ከሌሎች በርካታ አፍሪካ አገሮች ልምድ በመነሳት ስለተደመደመ ነው፡፡ለዚህ ነው ሁሉም ነገር ለልማት አጀንዳው ተገዥ መሆን ያለበት፡፡ራሳችንን የመከላከል አቅማችን ደካማ ከሆነም የውጭና የመንደር ጎረምሶች ሁሉ ሳይቀር ሊገዳደሩን ይችላል፡፡ለምሳሌ አዲሲቱን ኢትዮጵያ መፍጠር ሲባል ምን ማለት ነው የሚለው እያንዳንዳችን ከዚህ ጋር ተያይዞ ባለን ጥብቅ ግንኙነትና የተለየ ጥቅም ምክንያት ሚዛን የሚደፋ ርእስ ነው፡፡

አዲስቱ ኢትዮጵያ እንፍጠር ሲባል የቆየውን ኢትዮጵያዊነት ወደጎን በማድረግ ቅንጣት ታክል ነገር እንኳ ሳንወስድ በጠቅላላው ከስር መሰረቱ ጥለነው መሄድ አለብን ማለት አይሆንም፡፡አብሮ በመኖር በጋራ የሚወሰድ ጥሩም መጥፎም የጋራ ተሞክሮ ስላለን፡፡ይህ የሚፈጥርልን የአንድነት መንፈስ አለ፡፡አብረን በመኖር መተዋወቅ፣መቀራረብ፣መተሳሰር አለ፡፡አብረን ለመኖርም ያለንን እምነት እና የወደፊት የጋራ እድል በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር በቀለማት ያሸበረቀ ተስፋችንን  በተመለከተ በየቀኑ ስንዘምርና በተግባር እያሳየን እዚህ ደርሰናል፡፡ይህ ለአዲሱ ኢትዮጵያዊነት ለመፍጠር ንጣፍና መሰረት የሚሆን እንጂ የሚጣል ነገር አይሆንም፡፡ሆኖም የቆየው አንድነታችን ጭቆና አልነበረበትም በአድልዎ ላይ የተመሰረተ መልክና ይዘት አልነበረውም ማለት አይደለም፡፡መጪው የጋራ እድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነው የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅም በማሳደግ እንጂ አዲሱ ኢትዮጵያዊነት ይህንን ጠጋግኖና አሻሽሎ ሊወርሰው አይችልም፣አይገባምም፡፡ጭቆና መኖሩን ማመን አፍአዊ አይደለም፡፡አዲሱ ኢትዮጵያዊነት ይዘት ከቆየው በአይነቱ የተለየና አድሎና ጭቆና ሙሉ በሙሉ ያስወገደ መሆን አለበት፡፡ እንደማንኛውም አዲስ ነገር ሁሉ አዲሱን ኢትዮጵያዊነት ከአሮጌው የተወሰኑ ነገሮችን በመውረስ ግን ደግሞ በአሮጌው መካነ መቃብር ላይ መሆን እንዳለበት እስማማለሁ፡፡

የአሁኑ ስርአት ችግር  አመራሮቹ በምቾትና በስሜት በመሸነፍ የመዘናጋት ጉዳይ ካልሆነ በቀር ከቀድሞ ጋር የሚነጻጸር አይደለም፡፡የቀድሞ ስርአት በደል አድርሷል ሲባል ግን ስለተገደሉት ብቻ ማንጎራጎር ሳይሆን ከፍተኛ አደጋ የደረሰው ከሞት በተረፉትና የስነልቦና ቀውስ በደረሰባቸው ወገኖቻችን ላይ መሆኑና በዚያን ጊዜ የተዘራው መርዝ ደግሞ በሌላው ላይ ሁሉ ሳይቀር ተጽእኖ በማሳድር ያንን ክፉ ነቀርሳ ነቅለው ለመጣል እስካሁንም የተቸገሩ ምናልባትም እንደ ጃዋር ያሉ ለበቀል የተነሱ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ሆኖም በቅድሚያ እያንዳንዳችን በግለሰብ ደረጃ በማንነታችን የመኩራትና ባህላችንን ማዳበር እንደሚገባ የታወቀ ነው፡፡

እኛ ማንነታችንን ያልተንከባከብነውን ማነንነታችንን  ሌሎች ውሃ እያጠጡ ሊኮተኩቱልን አይችሉም፡፡ታዲያ ይህ ስርአት ያደረገውም ምንድን ነው? እንደማንኛውም ስርአት የራሱ ችግር ቢኖርበት አያስደንቅም፡፡በየትኛውም ስርአት ያላየነውን ተአምረኛ የኢኮኖሚ ለውጥ ያመጣ ስርአትን፣ለሚሰራቸው ጥፋቶች ቢኖሩ ካለማወላወል አምኖ ለማስተካከል የሚታትር ለሌሎች አገሮች ምሳሌ የሚሆን ስርአትን በህዝብ ላይ ጦር ሰብቆ እንደዘመተ ማስመሰል በራሱ ከማስመሰል የዘለለ አይሆንም፡፡

ለምሳሌ ይህ ስርአት እንደ ስርአት የማንንም ባህላዊ ስርአት አላጠፋም፤ለእድገቱ የማይበጅና ስርአትም አልጫነበትም፣እንደ በቅሎ አልተፈናጠጠበትም፣እለት ተእለት እንደሚያደርጉት የደርግ ገራፊዎች ገልብጦ ስጋውን አልተለተለውም፣በእሳት አልጠበሰውም፣በጥቅሉ በስብእናው ላይ አልዘመተበትም፣ይልቁንስ ባህሉና ቋንቋው እንዲዳድብር እራሱን በራሱ በአብራኩ ክፋይ ልጆቹ እንዲተዳደር እንጂ እንደቀድሞው ጥፍሩ እየተነቀለ፣የገማ ውሃ ውስጥ ጭንቅላቱን ነክሮ አሳሩን አላበላውም፣ይሄንን ጀግና ህዝብ ተጠራጣሪ እንዲሆን አላደረገውም፡፡ስለዚህ አንዳንዱ ሞትን እንዲንቅ ኑሮውን እንዲጠላ የበቀል ስሜት እንዲያረግዝና ቁጣውን እንደ ሰደድ እሳት በማያያዝ ያገኘውን ለማቃጠል ደረጃ አድርሶታል ብዬ አላምንም፡፡ይልቁንስ እነ ጃዋር እና የነጋ ልጆች አንዳንዱን በጥቅም በመደለል ክንፍ እንዳለው ነጭ አህያ በላዩ ላይ ወጥተው ሲያበቁ በሉጓም አስረውት በደስታ ሲጋልቡት፣አስራ ሶስት ክንፍ ያለው መልአከ ሞት ሲያስልኩበትና ሞት ጥቁር ክንፉን እየዘረጋበት ሰማያዊ የሃር ብርድ ልብስ እስኪመስለው ድረስ በ‹ኢሳት› ሰበካቸው አዘናግተው እንደሚታጠብ ጋቢ አንገቱን ጠምዝዘው በደስታ ቼ ሲሉት እውን የትኛውን የተጋረደ ዓይኑን ገልጠውለት ይሆን የሚጋለብ እላለሁ፡፡

<u>የህዝባዊ አንድነትና ጥሩ ትዳር መመሳሰል</u>

በመሰረቱ ህዝባዊ አንድነትና ጥሩ ትዳር የሚያመሳስሉዋቸው ብቁ ነገሮች አሉ፡፡ሁለቱም ዝምድናዎች በመሰረቱ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረቱ፣የጋራ ጥቅም በሌለበት ወቅት ደግሞ የሚበተኑ ስለሆኑ ኮንትራታዊ ባህሪ ያላቸው ዝምድናዎች ናቸው፡፡

ይህ ግን የዝምድናውን አንድ መሰረታዊ ባህሪ የሚገልጽ እንጂ ዝምድናውን በኮንትራታዊ ዝምድና ብቻ የታጠረ መሆኑን የሚያመለክት ነገር አይደለም፡፡ፍቅርና መተሳሰብ የተሞላበት ቤተሰባዊ መንፈስም የዝምድናው ሌላ መሰረታዊ ባህሪ ነው፡፡ኮንትራታዊ ብቻ ከሆነ ጠንካራ አንድነት ወይም ጥሩ ትዳር ሊሆን አይችልም፡፡በሌላ በኩል የጋራ ጥቅምን የማያረጋግጥ ከሆነ ፍቅርና ስምምነት የተሞላበት መሆን አይችልም፡፡ሁለቱንም አጠምሮ የያዘ ትዳር ብቻ ነው ጥሩ ቤተሰብንና ትዳርን መፍጠር የሚችለው፡፡ይህች አገር እነዚህን ሁለቱን አጣምራ የያዘች እንደሆነ ይታመናል፡፡

ይሁን እንጂ በመድረክ ወጥተው በተግባር የምናያቸው አንዳንድ አመለካከቶች የኛ አይደለም የሚሉትን ህዝብ እንደ ህዝብ መጠን በመናቅ፣በመጥላትና በመቃወም የኛነው የሚሉትን ህዝብ ደግሞ በባህሪው ከሌላው የበለጠና የበላይ አድርጎ በመውሰድ የሚገለጹ አመለካከቶች ናቸው፡፡እነዚህ አመለካከቶች ስያሜ እንስጣቸው ቢባል ከአፍራሽ ትርጉማቸው አንጻር ለምሳሌ የጠባብነትና ትምክህተኛ አመለካከቶች ልንላቸው እንችላለን፡፡

እነዚህ አፍራሽ አመለካከቶች በህዝቦች መካከል ጠንካራ አንድነት እንዳይኖር የሚያደርጉ ካንሰሮች ናቸው፡፡ለዚህ ነው የዚህ አስተሳሰብ ተሸካሚ የሆነ ሰው ከዚህ እንዲላቀቅ ብርቱ ጥረት ያስፈልጋል የሚባለው፡፡ይህ ሲባል የሰዎችን ብሄራዊ ማንነት በማየት ጥሩዎች ወይም መጥፎዎች ወይ ደግሞ ጠላቶች ብሎ መመደብ እንደማይገባ የታመነ ነው፡፡

ሆኖም እነዚህ አስተሳሰቦች የበላይ ሆነው እስካሉ ግን ኢትዮጵዊነትም ሆነ የህዝቦች አንድነት ለመኖር ፈተናዎች ሆነው መቀጠላቸው አይቀርም፡፡እነዚህን መዋጋት የሚያስፈልገው በጉዟችን በሚፈጥረው እንቅፋት ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡

በአጭሩ አዲስ ኢትዮጵያዊነት መፍጠር ስንል በህዝቦች መተሳሰብ፣መፈቃቀድና መከባበር ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲኖር፣ለዚህም ደግሞ አሁን ባለንበት ወቅት እንደዚህ አይነት ዝምድና በህዝቦች ውስጥ እንዳይኖር እንቅፋት ሆነው የሚገኙትነ ጠባብነትና ትምክህትን በመታገል ላይ የተሞረኮዘ አንድነት መፍጠር ይገባል ማለት ነው፡፡

<u>የወረስናት ኢትዮጵያ ምን ትመስል ነበር?</u>

አዲሱ ኢትዮጵያዊነት የኢትዮጵያን ህዝብ ሃቀኛ ታሪክ ከስር መሰረቱ ያሳያል፡፡የወረስነው ኢትዮጵያዊነት የመላውን የኢትዮጵያ ህዝብ እውነተኛ ታሪክ ማለትም ጥሩውንም ይሁን መጥፎውን በትክክል አስቀምጦ ህዝቡ ከጥሩውም ይሁን ከመጥፎው በሚገባ ተምሮ በዚህ ላይ የተመሰረተ ቤተሰባዊ መንፈስ እንዲፈጠር የሚያደርግ ሳይሆን የታሪኩን የተወሰነ ክፋይ ቆንጽሎ በመውሰድ፣በብዙ አፈ-ታሪክ የተሞላውን የገዥዎችን ጥቅምና እምነት የሚያንጸባርቀውን ታሪክ ነበር የኢትዮጵያ ህዝብ ሃቀኛ ታሪክ ብሎ ሲቀርብ የቆየው፡፡

የወረስነው ኢትዮጵያዊነት ኢትዮጵያ ብዙ ቋንቋ፣ባህል፣ያላት መሆኑን አንድ ጳጋና የጠንካራ አንድነት ምንጭ አድርጎ የሚወስድ አልነበረም፡፡ይህን ልዩነት የሚያቅፍ፣የሚያስተናግድና መሰረት የሚያደርግ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት ሳይሆን ይህን ልዩነት እንደ ትልቅ ደካማ ጎንና የአደጋ ምንጭ አድርጎ መውሰድ ነበር፡፡ለዚህም ሲባል ሃብታም ከሆነው ባህላችንና ቋንቋችን ጨልፎ በመውሰድ እንደብቸኛ የኢትዮጵያ ቋንቋና ባህል አድርጎ ለመጫን ነው ይሰራ የነበረው፡፡ለምሳሌ አማርኛ ማወቅ እንደ ልዩ እውቀት ተቆጥሮ ባለፉት ዘመናት ሁሉ አፈር ድሜ የበሉ ብዙ ናቸው፡፡ባለፈው ዘመን አማርኛ መናገር ለሚቸገረው አንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብና ህዝብ‹ገመድ አፍ‹የሚል ስያሜ ታፔላ ቢለጥፉም አማርኛ ሲያገለግል የኖረው ግን እስከ ስድስተኛ ክፍል ነበር፡፡ከዚያ በኋላ ከሰባተኛ ክፍል ጀምሮ ደግሞ ብዙዎቻችን እንግሊዝኛው ሲመጣ ለዚህኛው ደግሞ ‹ገመድ አፍ ›ሆንን ማለት ነው፡፡ትምክህተኞችና ጠባቦች ሰይጣናዊ ባህሪይ የተላበሱ በነርሱ የንቀትና የጥላቻ ዝባዝንኬ እየተገፋን የህዝብ ጥቅም በሚጎዳ አፍራሽ መንገድ እንድንሄድ ሌት ከቀን ያለእረፍት የሚሰሩና የሚጸልዩ ናቸው፡፡እነሱ ከጻፉት በላይ ሊናገሩ እንደመይችሉ የታመነ ነው፡፡ለምሳሌ ዝርዝሩን ትተን በጥቂቱ የአለቃ ኪዳነወለድ መዝገበ ቃላት ማየት ለአንባቢ ይበቃዋል፡፡

<u>የአዲሲቱ ኢትዮጵያ መገለጫ</u>

አዲሱ ኢትዮጸያዊነት የኢትዮጵያ ታሪክ የሁሉም ህዝቦች የዝምድና ታሪክ ድምር እንጂ ተቆንጥሮ የሚወሰድ፣ ጥሩ የሆነው ብቻ የሚቀርብበት አፈ-ታሪክ እንዳልሆነ የሚቆጥር ነገር ግን የኢትዮጵያን ቋንቋ፣ባህል፣ወ.ዘ.ተ.የሁሉም ህዝብ የቋንቋ፣የታሪክ፣ድምር መሆኑን የሚቀበል፣ይህንን ነባራዊ ልዩነት የሚያስተናግድ፣የሚያቅፍ፣በተግባርም ይህን መሰረት ያደረገ አንድነትን የሚፈጥር መሆን አለበት፡፡

‹አዲሲቱ ኢትዮጵያ ስንል ህዝቦቿ ከ ሺ ዓመት በፊት ደርሰውበት የነበረውን ስልጣኔ ደረጃ ማድነቃችን፣በዚሁ ውጤት መኩራታችንና ቆርጠን መነሳታችንን መግለጻችን ማለት ነው፡፡ገናናውን የህዝቦቻችንን ታሪክ ለመድገም መከጀላችንን የሚያሳይ ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ ገናና ታሪካችን ሂደት ብዝሃነታችንን ማስተናገድ ተስኖን፣ልማቱን የሚያፋጥን አመራር መፍጠር አቅቶን ከተሰፈኞችና ለማኞች ጎራ የተሰልፍንበትን የውርደት ታሪካችን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አስወግደን አዲስና ገናና ታሪክ ለመጻፍ ቆርጠን መነሳታችንን ማመላከታችንም ነው፡፡ካለፈው ታሪክም በላይ የወደፊት ጉዞውን ማመላከታችንም ነው፡፡›

<u>የአዲሲቱ ኢትዮጵያ በለውጥ ጉዞ ላይ</u>

‹ፈረንጆች የማይለወጥ ነገር ቢኖር ለውጥ አይቀሬ መሆኑ ብቻ ነው ይላሉ፡፡ከድህነት ወደ ብልጽግና የሚደረገው ጉዞ ብዙ ለውጥ ብቻ ሳይሆን ፈጣን ለውጥ የሚታይበት ሂደት ነው፡፡የለውጥ ሂደቱ ሲያዘግም ጉዞው ለአደጋ ይጋለጣል፡፡የምንመኛት አዲሲቱ ኢትዮጵያ እውን የምትሆነው ከኢኮኖሚ እድገት አንጻር ቢታይ ከድህነት አዙሪት ወጥተን የነፍስ ወከፍ ገቢያችን ቢያንስ 10000 ዶላር ሲደርስ ነው፡፡ኪራይ ሰብሳቢዎች ግን ካደረጉት አስተዋጽኦ በላይ ይህንን አረጋግጠው በምቾት እየኖሩ የእነሱ ትግል ይህን ጥቅማቸውን ለማስቀጠልና ለማስጠበቅ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

በብዙሃኑ አስተሳሰብ ግን እስካሁን ከሄድንበት የጊዜ ርዝመት ተጨማሪ 30-40 አመት በመጠበቅ ልንደርስበት የምንችለው ይሆናል የሚል አመለካከት አለ፡፡ይህ ሊሆን የሚችለው ፈጣን እድገቱ ሲቀጥልና፣ፈጣን እድገቱ ያልተቆራረጠና ቀጣይነቱ የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው፡፡በእርግጥ በተመሳሳይ አቅጣጫ መቀጠል እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዜጎች ጉዞውን ሳይጀምሩ ወይም በመሃል ቢታክታቸውና ተስፋ ቢቆርጡ የሚገርም አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል የእድገት ሂደቱ ማንኛውም ዜጋ ጥሎ የማይጥል መሆኑ ማረጋገጥ ካልተቻለ ስጋቱና ጥርጣሬው በአጥጋቢ ሁኔታ ሊወገድ አይችልም፡፡ወጣቱ ይህች አገር አደገች አላደገች ምኔ ናት? የሃብት ክፍፍሉ ተጠቃሚ አልሆንኩም፣ ስራ ፈት ሆኛለሁ ካለ በቂ ምክንያት አለው፡፡በዚህ ረገድ ችግሩን ተረድቶ ፈጣን ምላሽ መስጠቱና ቁርጠኝነት መታየቱ እርካታን የሚፈጥር ነው፡፡የእድገት ፈጣን ባቡር በሚንቀሳቀስበት ወቅት ሁሉም ዜጎች ተሳፋሪ እንደሚሆኑና ማንኛውም ዜጋ ለለውጥ ዝግጁና የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያደርግ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡በጋራ የምንጓዘው ተመሳሳይ ዓላማና ግብ ስላለንና እስካለን ድረስ ብቻ ነው፡፡ስለተማማልን ወይም ስለተዛመድን አይደለም፡፡

ለአንድ ረጅም የማራቶን ሩጫ ሳይሆን በዱላ ቅብብሎሽ መልክ ለሚከናወኑ በርካታ የማራቶን ሩጫዎች መሰለፍ ማለት ነው፡፡ትውልዶች፣ፓርቲዎች ቢቀያየሩም ዋናው ጉዳይ ጥርጊያው በመሰረቱ በዳበረ ዴሞክራሲ እድገት መስመሩ መቀጠሉ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

<u>አዲሱ ኢትዮጵያዊነት ሊያብብና ሊሰፋ የሚችለው</u>

ቀደም ሲል እንደተባለው በአንድ በኩል የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ስር እንዲሰድ ለማድረግ በጠባብነትና ትምክህት ላይ ትግል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ትግሉ ደግሞ ግቡን ሊመታ የሚችለው የአስተሳሰቡ ምንጭና ዋነኛ ተጠቃሚዎች እነማን እንደሆኑ ተለይቶ በእነሱ ላይ ያተኮረና እነሱን በመነጠል የሚያተኩር ሲሆን ነው፡፡ይህ ማለት የትምክህትና የጠባብነት አስተሳሰብ ምንጭ ምን መሆኑን በመለየት ከስር መሰረታቸው የመንቀል አቅጣጫ መከተል እንጂ እስካሁን እንደተደረገው ቅርንጫፍ የሆኑትን ሃሳቦች እያረሙ መኖር አይደለም፡፡

ህዝብ በእንቅስቃሴ ውስጥ በስፋት እንዲሳተፍ የሚችላውና የሚነሳሳው፣በጣም የሚሰማውና ጥቅሙን የሚነካው ጉዳይ ሲያጋጥመው ነው፡፡ለምሳሌ በረሃብ የሚጠቃ አካባቢ ስላለ በሀገራችን ረሃብን ለማስወገድ እንንቀሳቀስ ቢባል ህዝቡን ከጫፍ እስከጫፍ በፍላጎትና በወኔ ማንቀሳቀስ እንደሚቻል የታወቀ ነው፡፡

እባብ እንዳይፈልስ ለማድረግ የህዝብ እንቅስቃሴ እናድርግ ቢባል ተግባሩ ላይ የሚሳተፍ ሰው በፍጹም አይኖርም ባይባልም እንዳገራችን ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ይህን የሚመለከት እንቅስቃሴ ማድረግ የሚታሰብ አይደለም፡፡

ብቁ የእንቅስቃሴ አመራር እንዲኖር ማድረግ ማለት በእንቅስቃሴው መሳተፍ ያለበት የህብረተሰብ አካል የሚሰማውንና የሚያነሳሳውን ግልጽ ጥያቄ ማንሳትና የዚህም ግብ ማስቀመጥ፣ዓላማና ግቡን በጥንቃቄ መምረጥ ማለት ነው፡፡ህዝቡን የሚያነሳሳ ጥያቄ ሳይያዝ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ቀጣይ እንቅስቃሴ ማነሳሳት አይቻልም፡፡ይህን የመሰለ ጥያቄም ተይዞ ቢሆን ህዝብን አያንቀሳቅስም፡፡ስለዚህ እንቅስቃሴን በብቃት መምራት ማለት ከሁሉም በፊት ህዝቡን ሊያነሳሳና በአቅሙ ሊፈጸም የሚችል አላማና ግብ በጥንቃቄ መለየት ማለት ነው፡፡ቀጥሎ የሚመጣው የእንቅስቃሴ አመራር ብቃት ጉዳይ በተቀመጠው አላማና ግብ ዙሪያ ተሳታፊውን ማሰባሰብ መቻል ነው፡፡ተሳታፊ ማሰባሰብ ሲባል ተጠቃሚውን የሚሆን ተሳታፊ ማሰባሰብ ማለት ነው፡፡

በህብረተሰቡ ውስጥ የተጀመረውን የለውጥ ማእበል እንቅስቃሴ ይሁን በኪራይሰብሳቢነት ላይ የተከፈተው ዘመቻ የሚፋጠንበትን አቅጣጫ የሚወስነውን ገዥ መሬት የያዘው ገዢው ፓርቲ ነው፡፡የዚህ ማእበል ዋነኛ ኃይል የሆነውን ህዝብ የሚመራውና የሚያንቀሳቅሰውም ገዢው ፓርቲ ነው፡፡ህብረተሰቡ ካለበት ችግር ለመውጣት የሚችልበት መሰረታዊ ስልጣን ስትራተጂ ያለውም ገዢው ፓርቲ ነው፡፡እነዚህን ሶስት መሰረታዊ ነገሮች ደምረን ነው መሰረታዊ ባህሪ የሚወስነውን እንቅስቃሴ ለማቀጣጠል የሚሰራው፡፡ስለዚህ የሚያስፈልገው ገዢ መሬቱን መያዝ እንጂ ከንጹህ ውሃ በቀር ምንም ነገር ከፈጠርነው ማእበል ጋር መቀላቀል የለበትም ማለትም የለብንም!

እንግዲህ በህዝባዊ እንቅስቃሴ ትግሉ ቀጣይነት ባለው መንገድ የትምክህትና የጠባብነትን መልኮች እያስተካከለ የሚሄድ መሆን አለበት፡፡በሌላ በኩል የአዲሱን ኢትዮጵያዊነት ይዘት ዘርዝሮ ማስቀመጥና ማስረጽ ይጠይቃል፡፡በመሰረቱ አዲሱ ኢትዮጵያዊነት በይበልጥ ነባራዊ በሆነው የጋራ ተሞክሮ ላይ እንደሚመሰረት የታወቀ ነው፡፡ይሁን እንጂ ይህ የጋራ ተሞክሮ ተነጣጥሎ የሚከናወን በመሆኑ በጋራ ለማቀናጀት የሚያስችሉ መድረኮችና ቅኝት ስለሌለው አስፈላጊውን መንፈስ በመፍጠር ላይ መጫወት የሚገባውን ሚና ተጫውተ አልልም፡፡ለምሳሌ አንድ ኢኮኖሚያዊ መሰረት ለመፍጠር የሚካሄድ ስራ እንኳ ቢኖርም ዛሬም ከ25 ዓመት በኃላ ከችግሮች ነጻ ሊባል አይችልም፡፡ኢትዮጵያን በሙሉ የሚያካትት አንድ ኢኮኖሚያዊ መሰረት መኖሩ የተደላደለ ህዝባዊ አንድነት ከመፍጠር አንጻር ትልቅ ሚና እንዳለው የታወቀ ነው፡፡

ስለዚህ የሰላሳ እና አርባ ወይም አርባ እና ሃምሳ ዓመት ጉዞ ስኬት የሚወስነው ቁልፉ ጉዳይ በረጅም የለውጥና የትራንስፎርሜሽን ጉዞ ሂደት ውስጥ የዴሞክራሲን ቀጣይነት ሲረጋገጥ ነው፡፡በወዲፊት የአዲሲቱ ኢትዮጵያዊነት ይዘት ምን ሊሆን ይችላል? የተቀመጡት በርካታ ቁም ነገሮች የታላቁ መሪ ሌጋሲ ቢሆኑም እውን የአስተሳሰብ ልእልናው ተጠብቆ የህዝቡን ሃብትና ባህሉ እንዲያደርገው ተሰርቷልን?

በእውቀቱ ሲንጅ